# የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ

## ግላዊነትዎን ለመጠበቅ እንተጋለን

በCorewell Health ውስጥ የጤና መረጃዎ ግላዊነት ሁልጊዜም ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ይህ ማስታወቂያ ለCorewell Health ታካሚዎች እና ቤተሰቦች ስለ ግላዊነት መብቶቻቸው እና እነዚህን መብቶችን ማስጠበቅን በተመለከተ የCorewell Health ቀጣይነት ያለው ቁርጠኝነት ይገልጻል። የጤና መረጃዎ ስለሚሰበሰብበት እና ጥቅም ላይ ስለሚውልበት መንገድ በተመለከተ ምርጫዎች የመምረጥ መብት አለዎት።

## ለጥያቄዎች ወይም ማወቅ ለሚፈልጓቸው ጉዳዮች

Corewell Health, Chief Privacy Officer MC168,
100 Michigan Street NE, Grand Rapids, MI 49503

- በዚህ ቁጥር ይደውሉ: **616.486.4113**
- ኢሜይል: **privacy@corewellhealth.org**

## የግላዊነት አሰራሮችን በተመለከተ የጋራ ማስታወቂያ

ይህ ማስታወቂያ እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃ እንዴት ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል እና እንዴት ለሌላ ወገን ግልጽ ሊሆን እንደሚችል እና ይህን መረጃ እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ ይገልጻል። **እባክዎ ይህን ማስታወቂያ በጥንቃቄ ይመልከቱት።** ይህ ማስታወቂያ ከነሐሴ 17, 2023 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ይህን ማስታወቂያ በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎ እባክዎ የCorewell Health ዋና የግላዊነት መኮንንን በ**privacy@corewellhealth.org** ወይም ከላይ የተገለፀውን የግንኙነት መረጃ በመጠቀም ያነጋግሩ።

## ይህን ማስታወቂያ መከተል ያለበት ማን ነው

ይህ ማስታወቂያ ሆስፒታሎችን፣ የሰለጠኑ የቤት ውስጥ ህክምና እንክብካቤ ተቋማትን፣ የአስቸኳይ ህክምና ማዕከላትን፣ የህክምና ሰራተኞቻችንን፣ የቤት ለቤት የጤና እንክብካቤ ድርጅቶችን፣ ለሞት በሚያደርስ ህመም የተጠቁ ታካሚዎች የሚታከሙበት ተቋምን፣ ክሊኒኮችን፣ ቢሮዎችን፣ እና በCorewell Health ስር የሚተዳደሩ ተቋማትን ጨምሮ በ"Corewell Health" ወይም "የCorewell Health ተቋማት" ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ሁሉም የCorewell Health ተቋማት እና ቢሮዎች የተጠቀሱ ቢሆኑም ባይሆኑም ይህን ማስታወቂያ መከተል አለባቸው። በዚህ የግላዊነት አሰራሮች ማስታወቂያ ላይ የሚደረግ ለውጥን እንክብካቤ በሚያገኙበት ቢሮ ወይም ተቋም በስልክ ቁጥር **616.486.4113** በመደወል ወይም በ **privacy@corewellhealth.org** ኢሜይል በመላክ ማግኘት ይችላሉ። ይህ ማስታወቂያ በተጨማሪም በCorewell Health የተቀናጀ የጤና እንክብካቤ አሰጣጥ(OHCA) ላይ በሚሳተፉ ድርጅቶች ላይም ተፈጻሚ ይሆናል። እነዚህ ድርጅቶች የእርስዎን የተጠበቀ የጤና መረጃ (PHI) ለህክምና፣ ክፍያ እና ለጤና እንክብካቤ ስራዎች ሲባል እርስ በርሳቸው ይለዋወጣሉ።

Corewell Health በየትኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት በOHCAው ተሳትፎ ላይ ለውጥ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው። ስለ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ የOHCA ተሳትፎ ሁኔታ በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት በስልክ ቁጥር **616.486.4113** ይደውሉ ወይም በ **privacy@corewellhealth.org** ኢሜይል ይላኩ።

## የእርስዎን የጤና መረጃ በተመለከተ የኛ ቃል ኪዳን

የጤና መረጃዎ የግልዎ እንደሆነ የምንገነዘብ በመሆኑ የመረጃውን ግላዊነት ለመጠበቅ እንተጋለን። እርስዎን በተመለከተ የምንጠቀመው፣ የምናዘጋጀው፣ የምንይዘው እና የምንገልጸው የጤና መረጃ እርስዎ ከሚያገኙት የአካል እና የአእምሮ ጤና እንክብካቤ ጋር ተያያዥነት ያለው ሊሆን ይችላል። ከCorewell Health ለሚያገኟቸው እንክብካቤና አገልግሎቶች መዝገብ እናዘጋጃለን። ይህ መዝገብ ለእርስዎ ጥራቱን የጠበቀ እንክብካቤ እንድናቀርብ እና የተወሰኑ የህግ መስፈርቶችን እንድናከብር ያስችለናል። ይህ ማስታወቂያ ከእርስዎ እንክብካቤ ጋር በተያያዘ በCorewell Health በኤሌክትሮኒክስ ወይም በወረቀት በሚያዙ በሁሉም መዝገቦች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። እንክብካቤ የሚያቀርብልዎ ሃኪም የCorewell Health ቡድን አባል ካልሆነ የህክምና መረጃዎን አጠቃቀም ወይም መገለጽ በተመለከተ የተለዩ ፖሊሲዎች ወይም ማስታወቂያዎች ሊኖሩት ይችላል። ይህ ማስታወቂያ የጤና መረጃዎ ጥቅም ላይ ስለሚውልባቸው ወይም ግልጽ ስለሚደረግባቸው መንገዶች ይነግርዎታል። ማስታወቂያው በተጨማሪም የጤና መረጃ አጠቃቀም እና ግልጽ መደረግን በተመለከተ ስላሉዎት መብቶች እና ስለ እኛ ግዴታዎች ይገልጻል።

የሚከተለውን ለማድረግ በህግ እንገደዳለን:

- የእርስዎን PHI ግላዊነትና ደህንነት እንድንጠብቅ።
- በዚህ ማስታወቂያ ላይ የተገለጹትን የግላዊነት አሰራሮች እንድንከተልና የማስታወቂያውን ኮፒ ለእርስዎ እንድንሰጥ።
- ደህንነቱ ባልተጠበቀ ጥብቅ የጤና መረጃ ላይ የሚፈጸም የሚስጥር አጠባበቅ ጥሰትን ለተጎጂ ግለሰቦች እንድናሳውቅ።

## የጤና መረጃዎን እንዴት እንደምንጠቀም እና ግልጽ እንደምናደርግ

በብዙ ሁኔታዎች የጤና መረጃዎን ያለ የእርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ሆኖም ከዚህ በታች ያልተገለጹ አጠቃቀሞች እና ገለጻዎች በእርስዎ ፍቃድ ብቻ መደረግ አለባቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች የጤና መረጃዎን ለመጠቀም ወይም ግልጽ ለማድረግ የእርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፡ መረጃዎን ያለ እርስዎ ፍቃድ በፍጹም አንሸጥም ወይም ለገበያ ዓላማዎች አንጠቀምም። የሚከተሉት ምድቦች የጤና መረጃን የምንጠቀምባቸውን እና ግልጽ የምናደርግባቸውን የተለያዩ መንገዶች ይገልጻሉ።

**ለሕክምና:** የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እና ለሌሎች እርስዎን ለሚያክሙዎት ባለሙያዎች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን።
ለምሳሌ ያክል፡ በመጎዳትዎ ምክንያት የሚያክምዎ ሃኪም ከሌላ የጤና ህክምና እንክብካቤ አቅራቢ ጋር ስለ አጠቃላይ የጤና ሁኔታዎ በተመለከተ ይጠይቃል።
የጤና መረጃዎን ለህክምና እንክብካቤ ቀጣይነት ዓላማዎች ሲባል ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። የተለያዩ የCorewell Health መምሪያዎች የተለያዩ የሚያስፈልጉዎትን ነገሮች እንደ የመድሃኒት ማዘዣ ወረቀቶች፣ የላብራቶሪ ምርመራዎች፣ ኤክስ ሬይ፣ ወይም ለህክምና ወይም ሪፈር እንዲደረጉ ለማስተባበር የጤና መረጃዎን ግልጽ ሊያደርጉ ይችላሉ።
የጤና መረጃዎን በCorewell Health ህክምና መከታተልዎን ተከትሎ በጤና እንክብካቤዎ ላይ ተሳታፊ ለሆኑ እንደ የቤተሰብ አባላት ወይም የቤት ለቤት የጤና እንክብካቤ ድርጅቶች ለመሳሰሉት ከCorewell Health ውጭ ለሆኑ ሰዎች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። የጤና መረጃዎን ለጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች ሪፈር ለተባሉበት ወይም ለተዛወሩበት ለሌላ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ልንገልጽ እንችላለን።
የሚያክሙዎት ከCorewell Health ውጭ የሆኑ የጤና እንክብካቤ

አቅራቢዎች ህክምናዎን በተመለከተ ውሳኔዎችን ለማሳለፍ በተቻለ መጠን እጅግ የተሟላ መረጃ ማግኘት አለባቸው። እነዚህ አቅራቢዎች ለዚህ ዓላማ ሲባል የኤሌክትሮኒክስ እና የወረቀት መዝገቦችዎን ከCorewell Health ሊያገኙ ይችላሉ። በተጨማሪም እነዚህ አቅራቢዎች እርስዎን ለህክምና ወደ Corewell Health ሪፈር በሚሉበት ጊዜ የህክምናዎን አካሄድን ለመከታተል መዝገቦችዎን እና የጤና መረጃዎን ሊያገኙ ይችላሉ። Corewell Health በእነዚህ ሁኔታዎች ወቅት የመዝገቦችዎን ግላዊነት እና ደህንነት ለመጠበቅ ስራ ላይ ያዋላቸው ሥነ ሥርዓቶችና ቴክኖሎጂ አሉት።

**ለክፍያ:** የጤና መረጃዎን እና ጤና ነክ ያልሆነ መረጃዎን እርስዎ ከCorewell Health ለሚያገኟቸው ህክምና እና አገልግሎቶች ለጤና ወጪ እቅዶች ወይም ሌሎች ድርጅቶችን ለማስከፈልና ክፍያ ለማግኘት ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ፡ እርስዎን የተመለከተ መረጃ ለጤና እንክብካቤዎ ወይም አገልግሎቶችዎ ክፍያ እንዲከፍልልዎት ለማድረግ ለጤና መድን ዋስትና ወጪ እቅድዎ ልንሰጥ እንችላለን። ለጤና ወጪ እቅድዎ ለሚወስዱት ቀጣይ ህክምና ቅድሚያ ፍቃድ ለማግኘት ወይም እቅድዎ ህክምናዎን የሚሸፍንልዎ ስለመሆን አለመሆኑ ለመወሰን ስለሚወስዱት ህክምና ልንነግር እንችላለን። አንዳንድ በCorewell Health የሚሰሩ አቅራቢዎች ለብቻው ክፍያ ስለሚያስከፍሉ ሲሆን ክፍያውን እና የክፍያ ሂደቱን ለማስተባበር ለእነዚህ አቅራቢዎች ከክፍያ ጋር ተያያዥነት ያለው መረጃ ልንሰጥ እንችላለን። በተጨማሪም ስለ ሂሳብዎ ለመወያየት ወይም የመድን ዋስትና ሽፋንዎን ለማረጋገጥ ወይም ይህን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ከእርስዎ ጋር በጽሁፍ ወይም በስልክ ግንኙነት ልናደርግ እንችላለን። ለተወሰነ የጤና እንክብካቤ አይነት ወይም አገልግሎት ሙሉ ክፍያ ከከፈሉ እና የጤና ወጪ ዕቅድዎ ስለዚህ ህክምና አይነት ወይም አገልግሎት በተመለከተ መረጃ እንዲያገኝ እንደማይፈልጉ ከነገሩን ይህን መረጃ እንድንገልጽ በህግ ካልተገደድን በስተቀር ለጤና ወጪ ዕቅድዎ አንገልጽም።

**ለጤና እንክብካቤ ስራዎች:** የጤና መረጃዎን ስራችንን ለማከናወን ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን—ለምሳሌ፡ ለሂሳብ ስራ፣ የክፍያ ጥያቄ ለማሰናዳት ወይም ሰራተኛ ኃይላችንን ለመገምገም። እነዚህ መረጃ አጠቃቀሞች እና መረጃ ግልጽ የማድረግ ሂደቶች የCorewell Healthን የስራ እንቅስቃሴዎች ለማከናወን እና ሁሉም ታካሚዎቻችን ጥራቱን የጠበቀ እንክብካቤ እንዲያገኙ ለማረጋገጥ አስፈላጊ ናቸው። ለምሳሌ፡ መረጃዎን የCorewell Health የጤና እቅድ ለሆነው እና የተቀናጀ የጤና እንክብካቤ አሰጣጥ (OHCA) አንድ አካል ለሆነው ለPriority Health፣ ግለጽ ልናደርግ እንችላለን። መረጃን ከPriority Health ጋር መጋራት እንደ የጥራት ማሻሻያ፣ የህዝብ ጤና አስተዳደር እና የመሳሰሉትን የተቀናጀ የጤና ስርዓታችንን ዓላማዎችን ለማሳካት፣ እና Corewell Health እና Priority Health የሚያገለግሏቸውን ማህበረሰቦች አጠቃላይ ጤናና ደህንነት ለማሻሻል ይረዳናል። በተጨማሪም የተወሰኑ የህክምናና የህክምና ነክ ያልሆኑ መረጃዎችን እርስዎን ለማግኘት እና ከCorewell Health ስላገኟቸው አገልግሎቶች ጥራት እና አገልግሎቶቻችንን እንዴት ማሻሻል እንደምንችል በተመለከተ አስተያየትዎን ለማግኘት ልንጠቀም እንችላለን። በተጨማሪም Corewell Health ምን ምን ተጨማሪ አገልግሎቶችን ማቅረብ እንዳለበት፣ ምን ምን አገልግሎቶች እንደማያስፈልጉ፣ እና የተወሰኑ አዳዲስ ህክምናዎች ውጤታማ ስለመሆን አለመሆናቸው ለመወሰን የብዙ ታካሚዎች መረጃዎችን አንድ ላይ ልናጣምር እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪም መረጃን ለትምህርታዊ ዓላማዎች ሲባል ለሃኪሞች፣ ነርሶች፣ የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ተማሪዎች እና ለሌሎች የሆስፒታል ሰራተኞች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። እኛ ጋር ያለውን የጤና መረጃ አፈጻጸማችንን ለማነጻጸር እና እንዴት የምናቀርባቸውን እንክብካቤና አገልግሎቶች ማሻሻል እንደምንችል ለመወሰን ከሌሎች ድርጅቶች የጤና መረጃ ጋር አንድ ላይ ልናጣምር እንችላለን።

**ልዩ አጠቃቀሞችና መግለጾች:** የጤና መረጃዎን መረጃው በህግ ከሚፈቀድ ወይም ከሚጠየቅ ከሌላ አጠቃቀም ወይም አገላለጽ ጋር በሚገናኝበት ወቅት ልንጠቀም ወይም ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ፡ አንዳንድ ጊዜያት የህክምና ሁኔታዎን በተመለከተ በዶክተሮች፣ ነርሶች ወይም ሌሎች የCorewell Health ሰራተኞች መካከል ውይይቶች ሲደረጉ ሊደመጥ ይችላል። እባክዎ በተቻለ መጠን እነዚህን ሁኔታዎች ለማስቀረት ተገቢ ጥንቃቄዎችን የምናደርግ መሆኑን እርግጠኛ ይሁኑ።

**የቀጠሮ ማስታወሻዎች:** በCorewell Health ተቋም ያልዎትን ቀጣይ ቀጠሮ ወይም የታዘዘ መድሀኒትዎን እንደገና መሙላት የሚያስፈልግዎ መሆኑን ለማስታወስ የጤና መረጃዎን ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን።

**የገንዘብ ማሰባሰቢያ ስራዎች:** በገንዘብ ማሰባሰቢያ ወቅት ስምዎን፣ አድራሻዎን፣ ስልክ ቁጥርዎን፣ የአገልግሎት ቀናት እና ቦታን፣ ዕድሜን እና ጾታን ጨምሮ በእነዚህ ላይ ብቻ ሳይወሰን ሌሎች የተወሰኑ ህክምና ነክ ያልሆኑ መረጃዎችን ለCorewell Health ተባባሪዎች በCorewell Health ባለቤትነት በተያዘ ወይም ቁጥጥር በሚደረግበት ፋውንዴሽን በኩል ገንዘብ እንዲያሰባስቡ እርስዎን ለማነጋገር ልንጠቀም እንችላለን። የሚሰበሰበው ገንዘብ ለማህበረሰቡ የምናቀርባቸውን አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች ለማስፋፋትና ለማሻሻል ጥቅም ላይ ይውላል። የጤና መረጃዎ ለገንዘብ ማሰባሰቢያ ዓላማዎች ጥቅም ላይ እንዳይውል እና ግልጽ እንዳይደረግ “እራስዎትን የማግለል” መብት አልዎት።

**ለሆስፒታል ማውጫ:** እርስዎ በCorewell Health ሆስፒታል ታካሚ ሆነው ባሉበት ወቅት እርስዎን በተመለከተ የተወሰኑ መረጃዎችን በሆስፒታሉ ማውጫ ውስጥ ልናካትት እንችላለን። ይህ መረጃ ስምዎን፣ በሆስፒታል ውስጥ ያሉበትን ቦታ፣ አጠቃላይ ሁኔታዎን (ለምሳሌ፡ ጥሩ፣ የተረጋጋ፣ ወዘተ) እና የየትኛው ሀይማኖት ተከታይ እንደሆኑ ሊያጠቃልል ይችላል። ይህ መረጃ የትኛውን ሃይማኖት እንደሚከተሉ ከሚገልጽ መረጃ በስተቀር ስለ እርስዎ በስምዎ ለሚጠይቁ ሰዎች ግልጽ ሊደረግ ይችላል። በተጨማሪም ሆስፒታሉ የየትኛው ሃይማኖት ተከታይ እንደሆኑ የሚገልጽ የተለየ ማውጫ ሊያዘጋጅ እና ለሃይማኖት አባቶች ማውጫውን ግልጽ ሊያደርግ ይችላል። ይህ የሚደረገው ቤተሰብዎ፣ ጓደኞችዎ እና የሃይማኖት አባቶች ወደ ሆስፒታል መጥተው እንዲጠይቁዎ እና ስለ ሁኔታዎ እንዲያውቁ ለማስቻል ነው። በሆስፒታል ማውጫዎች ውስጥ የሚካተተው መረጃዎን እንድንገድብ (እንድንቀንስ ወይም እንዳናካትት) እኛን የመጠየቅ መብት አልዎት። ክልከላዎቹ እንዲተገበሩ ለመጠየቅ ይህን በምዝገባ ወቅት ለእኛ መንገር አለብዎት።

**በእንክብካቤዎ ወይም የእንክብካቤዎ ክፍያ ላይ ስለሚሳተፉ ግለሰቦች:** እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን እርስዎ እስካልተቃወሙ ድረስ፣ ወይም መረጃውን ግልጽ ማድረጉ ለእርስዎ ጠቃሚ እንደሆነ ካመንን በእንክብካቤዎ ላይ ተሳታፊ ለሆነ ጓደኛዎ ወይም የቤተሰብ አባልዎ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። መረጃውን በተጨማሪም ለሌላ በክፍያዎ ላይ ተሳታፊ ለሆነ ወይም ለእንክብካቤዎ ክፍያ እርዳታ ለሚያደርግ ሰው ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ለቤተሰብዎ እና ጓደኞችዎ ስለ ጠቅላላ ሁኔታዎ ልንነግር እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪም እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን ለቤተሰብዎ ስለ ሁኔታዎ፣ ያሉበትን የህመም ደረጃና ያሉበት ቦታ ለማሳወቅ ከአደጋ ለማገገም ጥረት እና እገዛ ለሚያደርግ ተቋም ልንገልጽ እንችላለን።

**ለምርምር/ጥናት:** በተወሰኑ ሁኔታዎች እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎችን ለምርምር/ጥናት ዓላማዎች ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ፡- አንድ የምርምር ፕሮጀክት አንድ አይነት መድሀኒት የሚወስዱ ታካሚዎችን ጤናና ማገገም ለተመሳሳይ ሁኔታ ሌላ አይነት መድሀኒት ከሚወስዱ ታካሚዎች ጋር በማነጻጸር መገምገምን ሊይዝ

ይችላል። ሁሉም የምርምር ፕሮጀክቶች ልዩ የፍቃድ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ያልፋሉ። ይህ አሰራር የታቀደውን የምርምር ፕሮጀክት እና የፕሮጀክቱን የጤና መረጃ አጠቃቀም ይገመግማል። ይህ አሰራር በተጨማሪም የምርምሩ ፍላጎቶች ከታካሚዎቻችን የጤና መረጃቸው ግላዊነት ፍላጎቶች ጋር ተመጣጣኝ መሆናቸውን ያረጋግጣል። ለምርምር/ጥናት የጤና መረጃ ከመጠቀማችን ወይም ግልጽ ከማድረጋችን በፊት ፕሮጀክቱ በዚህ የምርምር ፍቃድ አሰጣጥ አሰራር አማካኝነት ይገመገማል። ሆኖም እርስዎን የተመለከተ መርጃዎን የምርምር ፕሮጀክት ለማካሄድ ለሚዘጋጁ ሰዎች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ለምሳሌ፡ ተመራማሪዎች የሚገመግሙት የጤና መረጃ ከCorewell Health ውጪ እስካልወጣ ድረስ ልዩ የህክምና ፍላጎቶች ያሏቸው ታካሚዎችን እንዲያጠኑ ለማገዝ ለተመራማሪዎች መረጃ ልንገልጽ እንችላለን። ተመራማሪው ስምዎን፣ አድራሻዎን ወይም ሌላ የግል መረጃዎን የሚያይ ከሆነ፣ ወይም በCorewell Health ከምርምር ጋር ተያያዥነት ባለው እንክብካቤዎ ላይ የሚሳተፍ ከሆነ የእርስዎን ልዩ ፍቃድ መጠየቅ ሊያስፈልገን ይችላል።

**በህግ በሚጠየቀው መሰረት:** እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን በፌደራል፣ የግዛት ወይም የአካባቢ ህግ፣ ወይም ደንብ ስንጠየቅ ግልጽ እናድርጋለን። ለምሳሌ፡ የተወሰኑ ጉዳቶችን ወይም ህመሞችን ለህዝብ ጤና አጠባበቅ ሲባል ሪፖርት ለማድረግ እንገደዳለን።

**ከባድ የጤና ወይም የደህንነት ስጋትን ለመቀልበስ:** የጤና መረጃዎን የእርስዎን ወይም የህዝብን ወይም የሌላን ሰው ከባድ የጤናና ደህንነት ስጋትን ለመከላከል አስፈላጊ ሲሆን ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። መረጃዎን የምንገልጸው ስጋቱን ለመከላከል ማገዝ ለሚችል ሰው ብቻ ነው።

**የCorewell Healthን ፕሮግራሞች ወይም ምርቶች በተመለከተ የሚደረጉ ግንኙነቶች:** የጤና መረጃዎን ለእርስዎ ከጤናዎ ጋር ተያያዥነት ስላለው የCorewell Health ምርት ወይም አገልግሎት መረጃ ለመስጠት ልንጠቀም እና ልንገልጽ እንችላለን። ከዚህ በተጨማሪም የጤና መረጃዎን ከህክምናዎ፣ የጉዳይ አስተዳደርዎ ወይም የእንክብካቤዎ ማስተባበር ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ለእርስዎ መረጃ ለመስጠት፣ ወይም አማራጭ ህክምናዎችን፣ አቅራቢዎች ወይም የእንክብካቤ ቦታዎችን ለመግለጽ ልንጠቀም ወይም ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። አልፎ አልፎ ስለ ሌላ ኩባንያ ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ልንነግርዎ የምንችል ቢሆንም የጤና መረጃዎን ለእነዚህ ግንኙነቶች የምንጠቀመው ወይም የምንገልጸው በአካል ከመጡ ብቻ ነው።

**የጤና መረጃ ልውውጥ:** Corewell Health የመድሃኒት ትእዛዝ መረጃን ጨምሮ የጤና መረጃን መዝግቦ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ይልካል። የጤና መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የሚገለጸው በዚህ ማስታወቂያ ውስጥ ለተገለጹት አላማዎች ሆኖ በአካባቢ፣ የግዛት እና ብሔራዊ የመረጃ ልውውጦች ጥበቃ ይደረግለታል። Corewell Health የMiHINን (የሚቺጋን የጤና መረጃ ኔትወርክ) ጨምሮ በጤና መረጃ ልውውጦች ላይ የሚሳተፍ ሲሆን ወደፊት በሌሎች የመረጃ ልውውጦች ላይ ሊሳተፍ ይችላል። MiHIN መረጃ እንዴት በመረጃ ልውውጥ ጊዜ ሊገኝ እንደሚችል በተመለከተ ሕጎች ያሉት ሲሆን የዚህን መረጃ አጠቃቀም እና ግልጽ አደራረግ ይገድባል። ስለ MiHIN እና ስለ መረጃዎ በዚህ እና በሌላ የጤና መረጃ ልውውጦች ስለመላክ ጋር በተያያዘ ስላሉዎ መብቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በ **privacy@corewellhealth.org** ኢሜይል መላክ ይችላሉ።

**Epic's Care Everywhere:** የህክምና መዝገብዎ በEpic የኮምፒውተር ሶፍትዌር ፕሮግራም ውስጥ ይቀመጣል። የሚያገኙትን እንክብካቤ ለማሻሻል Corewell Health የጤና መዝገቦችዎን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ Epic's Care Everywhereን በመጠቀም ለሌሎች አቅራቢዎች ያጋራል። ይህን የምናደርገው Epicን የሚጠቀሙ እና እርስዎን የሚያክሙ ሌሎች የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎችን ወዲያውኑ የህክምና መረጃዎችን እንዲያዩ ለማስቻል ነው። Epicን በሚጠቀም በሌላ ሆስፒታል በሚመዘገቡበት ጊዜ የዛ ሆስፒታል የሚያክምዎ ዶክተር ከሆስፒታላችን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የህክምና መረጃ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል። ለምሳሌ፡ ለድንገተኛ ህክምና አንድ ሀኪም ከCorewell Health የህክምና መረጃዎ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ እንዲሰጠው ሊጠይቅ የሚችል ሲሆን ፍቃድ ካገኘ የላብራቶሪ ውጤቶችዎ ላይ ይመለከታል። የጤና መረጃዎን በዚህ መንገድ ማጋራት ሀኪሙ የበለጠ በመረጃ የተደገፉ የህክምና ውሳኔ እንዲያሳልፍ ያስችለዋል። እርስዎ በአሁኑ ወቅት በመረጃ ጠያቂው ሆስፒታል ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢ እንክብካቤ እያገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በስራ ላይ የዋሉ የማረጋገጫ ዘዴዎች አሉ። የህክምና እንክብካቤ አቅራቢዎች ለእርስዎ እንክብካቤ እያቀረቡ መሆኑን ለማረጋገጥ እርስዎን የተመለከተ በቂ መረጃ ማግኘት ያለባቸው ሲሆን እርስዎ በእነርሱ የኤሌክትሮኒክስ የህክምና መዝገብ ውስጥ በታካሚነት መመዝገብ አለብዎ። የጤና መረጃዎ እንደ HIV/AIDS፣ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች፣ የዘረመል መረጃ፣ የአእምሮ ጤና፣ የእጽ ሱስ፣ የዘረመል ምርመራ፣ ወዘተ የመሳሰሉ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ህመሞችን ሊይዝ የሚችል ሲሆን የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎች በህክምና መዝገብዎ ወይም በእኛ የጤና መረጃ ልውውጥ ውስጥ አይካተቱም። ከEpic's Care Everywhere ውስጥ "ለመውጣት" የሚፈልጉ ከሆነ እባክዎ የግላዊነት ቢሮችንን በዚህ ማስታወቂያ የመጀመሪያው ረድፍ ስር በተዘረዘሩት የስልክ ቁጥር ወይም የኢሜይል አድራሻ ያነጋግሩ።

**የጤና መረጃዎን እንዴት ልንጠቀም ወይም ግልጽ ልናደርግ እንደምንችል– ልዩ ሁኔታዎች**

በብዙ ሁኔታዎች የጤና መረጃዎን ያለ እርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ልንጠቀም እና ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ከዚህ በታች የተመለከቱት በልዩ ሁኔታዎች የጤና መረጃዎን እንዴት ልንጠቀም ወይም ግልጽ ልናደርግ እንደምንችል ያብራራሉ።

**የአካል ክፍል እና የቲሹ ልገሳ**: የአካል ክፍል ለጋሽ ከሆኑ የጤና መረጃን እንደ አስፈላጊነቱ የአካል ክፍል ለሚይዙ፣ ወይም የአካል ክፍል፣ የአይንና ቲሹ ንቅለ ተከላ ለሚያካሂዱ ድርጅቶች፣ ወይም የአካል ክፍል ልገሳ ባንክ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን።

**ወታደርና የቀድሞ ወታደሮች** : የጦር ሀይሎች አባል ከሆኑ እርስዎን የተመለከተ የህክምና መረጃዎን በወታደራዊ እዝ ባለስልጣናት በሚጠየቀው መሰረት ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። በተጨማሪም የውጭ አገር የውትድርና ሰራተኞችን የተመለከተ የጤና መረጃን ለሚመለከተው የውጭ አገር ወታደራዊ ባለስልጣን ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። አንድ የቤተሰብ አባሎ በውትድርና ውስጥ እያገለገለ ከሆነ በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን ለቤተሰብ አባልዎ ስለ ሁኔታዎ ለማሳወቅ ለጦር ሃይሎች ወይም እንደ ቀይ መስቀል ላሉ ፈቃድ ላላቸው ማህበራዊ አገልግሎት ሰጪዎች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን።

**የሰራተኞች ካሳ**: እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን ለሰራተኞች ካሳ ወይም ተመሳሳይ ፕሮግራሞች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። እነዚህ ፕሮግራሞች ከስራ ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጉዳቶች ወይም ህመሞች ጥቅማ ጥቅሞችን ያቀርባሉ።

**የህብረተሰብ ጤና ስጋቶች**: እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን የሚከተሉትን ጨምሮ ለህብረተሰብ ጤና ተግባሮች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን፡

- በሽታ፣ ጉዳት ወይም አካል ገዳተኝነትን ለመከላከል ወይም ለመቆጣጠር።
- ወሊድ እና ሞትን ሪፖርት ለማድረግ እና በበሽታ ምዝገባዎች ላይ ለመሳተፍ።
- የህጻናት ጥቃት ወይም በግዴለሽነት ማሳደግን ሪፖርት ለማድረግ።
- የመድሀኒቶች ወይም የምርቶች ችግሮች አጸፋዊ ምላሾችን ሪፖርት ለማድረግ።
- ለሰዎች የሚጠቀሟቸውን ምርቶች እንዲመልሱ መልእክቶችን ለማስተላለፍ።
- ለበሽታ ተጋልጦ ሊሆን የሚችል ወይም በበሽታ የመያዝ ስጋት ሊኖርበት ወይም በሽታ ወይም አንድን ሁኔታን ሊያስተላልፍ የሚችል ሰውን ያለበትን ሁኔታ ለማሳወቅ።
- አንድ ታካሚ የጥቃት፣ የቸልተኝነት ወይም የቤት ውስጥ ጥቃት ሰለባ እንደሆነ ካመንን ይህን ለሚመለከተው የመንግስት ባለስልጣን ለማሳወቅ። ይህን መረጃ ግልጽ የምናደርገው እርስዎ ከተስማሙ ወይም በህግ ስንጠየቅ ወይም ሲፈቀድልን ብቻ ነው።

**የጤና ቁጥጥር ተግባሮች**: የጤና መረጃን በህግ ለተፈቀዱ ተግባሮች ለጤና ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ልንገልጽ እንችላለን። እነዚህ የቁጥጥር ስራዎች ለምሳሌ ኦዲቶችን፣ ምርመራዎችን፣ ፍተሻዎችን እና የፍቃድ አሰጣጦችን ሊያካትት ይችላል። እነዚህ ስራዎች ለመንግስት የጤና እንክብካቤ ስርዓትን፣ የመንግስት ፕሮግራሞችን እና የፍትሀ ብሔር መብቶች ህጎች መከበርን ለመቆጣጠር አስፈላጊ ናቸው።

**ክሶች እና አለመግባባቶች**: በክስ ወይም አለመግባባት ውስጥ ከሆኑ እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን ለፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ትእዛዝ ምላሽ ለመስጠት ስንል ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። በተጨማሪም እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን ለፍርድ ቤት መጥሪያ፣ ለግኝት ጥያቄ ወይም በአለመግባባቱ ውስጥ ተሳታፊ በሆነ ሰው ለሚከናወን ሌላ ህጋዊ ዓላማ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን፣ ነገር ግን ይህን ግልጽ የምናደርገው በመገለጹ እርስዎ ከተስማሙ ብቻ ነው። ሆኖም የመግለጽ ጥያቄው በዳኛ ከተፈረመበት ወይም በፍርድ ቤት ከታዘዘ የእርስዎ ፍቃድ አያስፈልግም።

**የህግ ተፈጻሚነት**: በሚከተሉት ሁኔታዎች የጤና መረጃን ለህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን ግልጽ ልናደርግ እንችላለን፡
ለፍርድ ቤት ትእዛዝ፣ የፍርድ ቤት መጥሪያ፣ የእስር ማዘዣ፣ መጥሪያዎች ወይም ተመሳሳይ ሂደቶች ምላሽ ለመስጠት፣

- ተጠርጣሪን፣ ኮብላይን፣ የሰነድ ማስረጃን ወይም የጠፋን ሰው ለይቶ ለማወቅ ወይም የሚገኝበትን ቦታ ለማወቅ፣
- መረጃው የወንጀል ሰለባን የተመለከተ ከሆነ እና በተወሰኑ ሁኔታዎች ምክንያት መረጃውን ግልጽ ለማድረግ የሰውዬውን ስምምነት ማግኘት ካልቻልን፣
- በወንጀል ድርጊት ምክንያት እንደተከሰተ ስላመንንበት ሞት በተመለከተ፣
- በCorewell Health ተቋም ውስጥ የተፈጸመ የወንጀል ድርጊትን በተመለከተ፣ ወይም
- በአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች ወቅት ወንጀልን፣ ወንጀሉ የተፈጸመበትና ሰለባዎቹ የሚገኙበትን ቦታ፣ ወይም ወንጀሉን የፈጸመውን ሰው ማንነት (ዝርዝር መረጃ ወይም ቦታ) ሪፖርት ለማድረግ።

**ለአሟሟት አጣኚዎች፣ የህክምና መርማሪዎች እና የቀብር ዳይሬክተሮች:** የጤና መረጃን ለሞት አጣኚ ወይም የህክምና መርማሪ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ይህም ለምሳሌ የሟችን ማንነት ለመለየት ወይም የሞቱን መንስኤ ለመወሰን አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪም ታካሚዎችን የተመለከተ የጤና መረጃን እንደ አስፈላጊነቱ ለቀብር ዳይሬክተሮች ተግባሮቻቸውን እንዲያከናውኑ ለማስቻል ልንገልጽ እንችላለን።

**ለብሔራዊ የፀጥታና ደህንነት ተግባሮች:** የጤና መረጃዎትን ለፌደራል የደህንነት ኃላፊዎች፣ የደህንነት ምላሽ ኃላፊዎች እና ለሌሎች በሕግ የተፈቀዱ ፀጥታን የማስጠበቅ ተግባሮች ግልጽ ልናደርግ እንችላለን።

**ለፕሬዝዳንቱና ለሌሎች የጥበቃ አገልግሎቶች :** እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃን ስልጣን ለተሰጣቸው የፌደራል ባለስልጣናት ፕሬዝዳንቱን፣ ስልጣን የተሰጣቸው ሰዎችን፣ ወይም የውጭ አገር የመንግስት ኃላፊዎችን ለመከላከል ወይም ልዩ ምርመራዎችን ለማካሄድ እንዲችሉ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን።

**ታራሚዎች:** እርስዎ በማረሚያ ተቋም ውስጥ ታራሚ ከሆኑ ወይም በህግ አስፈጻሚ ባለስልጣን ቁጥጥር ስር ከሆኑ የጤና መረጃዎን ለማረሚያ ተቋሙ ወይም የህግ አስፈጻሚ ባለስልጣኑ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ይህን ግልጽ ማድረጉ ለተቋሙ ለእርስዎ የጤና እንክብካቤ ለማቅረብ፣ የእርስዎን ወይም የሌሎች ሰዎችን ጤናና ደህንነት ለመጠበቅ፣ ወይም በማረሚያ ተቋሙ ጤናና ደህንነትን ለማስጠበቅ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል።

**ለሶስተኛ ወገኖች:** የCorewell Health ህጋዊ አካልን ወክለው አገልግሎት እንዲሰጡ ኮንትራት ለተዋዋልንባቸው ለተወሰኑ ሶስተኛ ወገኖች የእርስዎን የጤና መረጃ ግልጽ ልናደርግ እንችላለን። ይህን ካደረግን ከዚህ ሶስተኛ ወገን ለመረጃዎ ጥበቃ የሚያደርግ መሆኑን በተመለከተ የጽሁፍ ማረጋገጫ እንጠይቃለን።

**ጥብቅ የሚስጥር መረጃ:** የተወሰኑ የጤና መረጃዎች ልዩ የግላዊነት ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል፤ ለምሳሌ፡ የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎች፣ ለአእምሮ ጤናና የእድገት አካልጉዳቶች የሚቀርቡ አገልግሎቶች፣ የአልኮል መጠጥ እና የእጽ ሱስ ህክምናና የመከላከል አገልግሎቶች፣ እና የተወሰኑ በሽታዎች። ጥብቅ የህክምና ሚስጥር መረጃዎትን የምንጠቀመው ወይም ግልጽ የምናደርገው በህግ በሚፈቀደው ወይም በሚጠየቀው መሰረት ወይም በእርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ብቻ ነው።

## የጤና መረጃዎትን በተመለከተ ያሉዎት መብቶች

**የመመርመር እና ኮፒ የመውሰድ መብት:** የህክምና መዝገብዎን እና ሌላ በእኛ የተያዘ የጤና መረጃዎትን ለማየት የመጠየቅ ወይም የኤሌክትሮኒክስ ወይም የወረቀት ኮፒ የማግኘት መብት አለዎት። የሚሰጥዎ መረጃ የህክምናና የክፍያ መዝገቦችን የሚይዝ ቢሆንም የትኛውንም የሳይኮቴራፒ ማስታወሻዎችን አያካትትም። ይህን እንዴት እንደሚያደርጉ የጤና መረጃ አስተዳደርን (HIM) ይጠይቁ። የጤና መረጃዎን ኮፒ ወይም ማጠቃለያ በአብዛኛው ጥያቄ ባቀረቡልን በ30 ቀናት ውስጥ እንሰጥዎታለን። ለዚህም ተመጣጣኝ እና ወጪን መሰረት ያደረገ ክፍያ ልናስከፍልዎ እንችላለን። በአንዳንድ እጅግ ውስን ሁኔታዎች የመመርመር እና ቅጂ የመውሰድ ጥያቄዎን ውድቅ ልናደርግ እንችላለን። የጤና መረጃዎትን ለማየት ከተከለከሉ ክልከላው እንዲመረመርልዎት ሊጠይቁ ይችላሉ። በCorewell Health የሚመረጥ ሌላ ፍቃድ የተሰጠው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ጥያቄዎትን እና ክልከላውን ይመረምራል። ምርመራውን የሚያካሂደው ሰው የመጀመሪያ ጥያቄዎትን ያልተቀበለው ሰው መሆን የለበትም። የምርመራውን ውጤት እናከብራለን። በምርምር ጥናት ተግባሮች ላይ እየተሳተፉ ከሆነ መረጃውን የማግኘት ክልከላዎች ላይ ከመሳተፍዎ በፊት በፈረሙት የፍቃድ መስጫ

ቅጽ ላይ እስከተስማሙ ድረስ ከምርምሩ ጋር ተያያዥ የሆኑ አንዳንድ የጤና መረጃዎትን የመመርመርና ኮፒ የመውሰድ ጥያቄዎን ውድቅ ልናደርግ እንችላለን። በተጨማሪም በሌላ መልኩ ህግ መረጃ የማግኘት መብት ልንከለክል እንችላለን።

**የማሻሻል መብት:** HIMን ትክክል እንዳልሆነ ወይም እንዳልተሟላ የሚያስቡትን እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃ እንዲስተካክል መጠየቅ ይችላሉ። ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ይጠይቁን። ጥያቄዎ “ውድቅ ሆኗል” ልንልዎ እንችላለን፣ ሆኖም ለምን ለምን ውድቅ እንዳደረግነው በ60 ቀናት ውስጥ በጽሁፍ እናሳውቅዎታለን። የማሻሻል ጥያቄዎን በጽሁፍ ካልቀረበ ወይም ጥያቄውን የሚደግፍ ምክንያት ካላካተተበት ውድቅ ልናደርገው እንችላለን። በተጨማሪም የሚከተለውን መረጃ እንድናሻሽል ከጠየቁን ጥያቄዎን ውድቅ ልናደርግ እንችላለን:

- መረጃውን ያዘጋጀው ግለሰብ ወይም ተቋም ማሻሻያውን ለማድረግ ከአሁን በኋላ የማይገኝ ካልሆነ በስተቀር በእኛ ያልተዘጋጀ መረጃ።
- በእኛ ወይም በCorewell Health ተቋም የተያዘ የጤና መረጃ አካል ካልሆነ።
- እንዲመረምሩ እና ኮፒ እንዲወስዱ የተፈቀደልዎ መረጃ አካል ካልሆነ።
- መረጃው ትክክል እና የተሟላ ከሆነ።

**የተሰጡ መግለጫዎች ዝርዝርን የማግኘት መብት:** የጤና መረጃዎን ጥያቄ ካቀረቡበት ቀን በፊት ባሉት ስድስት ዓመታት ውስጥ ግልጽ ያደረግንባቸውን ጊዜያት ብዛት፣ ለማን ግልጽ እንዳደረግን፤ ለምን ግልጽ እንዳደረግን የተመለከተ ዝርዝር (መዝገብ) ሊጠይቁን ይችላሉ። ይህን እንዴት እንደሚጠይቁ በተመለከተ HIMን ይጠይቁ። ከህክምና፣ ክፍያና የጤና እንክብካቤ ስራዎች መግለጫዎች እና የተወሰኑ ሌሎች መግለጫዎች (ለምሳሌ፡ ከትኛውም እርስዎ ግልጽ እንድናደርግ ከጠየቁን) በስተቀር ሁሉንም መግለጫዎች እናካትታለን። በዓመት አንድ ጊዜ የመዝገብ አያያዝ በነጻ የምንሰጥ ቢሆንም በ12 ወራት ውስጥ ሌላ እንድንሰጥዎ ከጠየቁን ተመጣጣኝ እና ወጪን መሰረት ያደረገ ክፍያ እናስከፍልዎታለን። ጥያቄዎ ዝርዝሩን በምን አይነት መልኩ እንድንሰጥዎ እንደሚፈልጉ ማመላከት አለበት (ለምሳሌ፡ በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክስ)።

**ክልከላዎች የመጠየቅ መብት:** የተወሰኑ የጤና መረጃዎችን ለህክምና፣ ለክፍያ ወይም ለሌሎች ስራዎቻችን እንዳንጠቀም ወይም ግልጽ እንዳናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ። ሙሉ የአገልግሎት ወይም የጤና እንክብካቤ ክፍያዎን ከኪስ አውጥተው (በእራስዎ ወጪ) ከከፈሉ ይህን መረጃ ለጤና መድን ዋስትና ሰጪዎ ግልጽ እንዳናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ። መረጃውን እንድንገልጽ ህግ ካላስገደደን፣ በእንክብካቤዎ ላይ ተጽእኖ የሚፈጥር ካልሆነ ወይም ጥያቄዎን ማክበር ካልቻልን በስተቀር “እሺ” እንልዎታለን።

**የሚስጥር ግንኙነቶችን የመጠየቅ መብት:** የጤና እንክብካቤ ጉዳዮችን በተመለከተ በተወሰኑ መንገዶች ወይም በተወሰነ ቦታ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት እንድናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ። ለምሳሌ:- በስራ ቦታዎ ላይ እያሉ ወይም በኢሜይል ብቻ ከእርስዎ ጋር ግንኙነት እንድናደርግ ሊጠይቁን ይችላሉ። በሁሉም አሳማኝ በሆኑ ጥያቄዎች እንስማማለን። ጥያቄውን በምዝገባ ወቅት ለታካሚ ተወካይዎ ወይም ለግላዊነት አጠባበቅ ቢሮ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ጥያቄዎን በጽሁፍ እንዲያቀርቡ ልንጠይቅዎ እንችላለን።

**የዚህን ማስታወቂያ የወረቀት ቅጂ የማግኘት መብት:** የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ በየትኛውም ጊዜ ሊጠይቁ ይችላሉ። ይህን ማስታወቂያ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለማግኘት ቢስማሙም እንኳ የወረቀት ቅጂ የማግኘት መብት አለዎት። የዚህን ማስታወቂያ ቅጂ ከድረገጻችን ላይ በ **corewellhealth.org/policies** ተጠቅመው ወይም ከየትኛውም የCorewell Health ተቋም ማግኘት ይችላሉ።

**በዚህ ማስታወቂያ ላይ የሚደረጉ ለውጦች**

በዚህ ማስታወቂያ ላይ ለውጥ የማድረግ መብታችን የተጠበቀ ነው። በተጨማሪም እርስዎን በተመለከተ ቀደም ሲል በያዝነው የጤና መረጃ ላይ እና በየትኛውም ወደፊት በምናገኘው መረጃ ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የተሻሻለ ማስታወቂያ የማዘጋጀት መብታችን የተጠበቀ ነው። የአሁኑን ማስታወቂያ ኮፒ በተቋሞቻችን፣ ቢሮዎቻችን እና ማስታወቂያው በሚሸፍናቸው ቦታዎች ላይ እንለጥፋለን። ማስታወቂያው ተፈጻሚ የሚሆንበትን ቀን ይይዛል። በተጨማሪም በጣም ወቅታዊ የሆነውን ማስታወቂያ ቅጂ በተቋሙ ወይም በቢሮው በሚመዘገቡበት ወቅት፣ ለህክምና ወይም የጤና እንክብካቤ አገልግሎቶች እንደ ተኝቶ ታካሚ ወይም ተመላላሽ ታካሚ ወደ ተቋም ወይም ቢሮ በሚመጡበት ወቅት ይሰጥዎታል።

የመረጃዎችዎ የግላዊነት መብቶችዎ እንደተጣሱ ካመኑ ለCorewell Health ወይም ለጤናና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሊያቀርቡ ይችላሉ።
ለCorewell Health ቅሬታ ለማስመዝገብ በኢሜይል
በ **privacy@corewellhealth.org** ይላኩ ወይም የሚከተለውን አድራሻ ይጠቀሙ:-
Corewell Health, Chief Privacy Officer MC168,
100 Michigan Street NE, Grand Rapids, MI 49503.

ሁሉም ቅሬታዎች በጽሁፍ መቅረብ አለባቸው።
ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት አይቀጡም።

**ሌሎች የጤና መረጃዎ አጠቃቀሞች**

በዚህ ማስታወቂያ ወይም በCorewell Health ላይ ተፈጻሚነት ባላቸው ህጎች ስር ያልተካተቱ ሌሎች የጤና መረጃ አጠቃቀሞችና መግለጾች የሚደረጉት በእርስዎ የጽሁፍ ፍቃድ ብቻ ነው። የህክምና መረጃዎን እንድንጠቀም ወይም እንድንገልጽ ፍቃድ ከሰጡን ፍቃዱን በየትኛውም ጊዜ በጽሁፍ መሻር ይችላሉ። ፍቃድዎን የሚሽሩ ከሆነ እርስዎን የተመለከተ የጤና መረጃዎን በጽሁፍ ፍቃድዎ ስር በተካተቱ ምክንያቶች አንጠቀምም ወይም ግልጽ አናደርግም። ቀደም ሲል በእርስዎ ፍቃድ የሰጠናቸውን የትኛውንም መግለጫዎች መቀየር የማንችል ከመሆኑም በተጨማሪ ለእርስዎ ላቀረብነው እንክብካቤ መዝገቦች እንድንይዝ እንገደዳለን።

**corewellhealth.org/policies**

Corewell Health © 10.2023